ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies (FSS)

ጥር 2003 ዓ.ም. **የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች** ቁጥር 27

# በኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉ ወቅታዊ የመወያያ ጉዳዮች

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም.ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፡፡

በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

በአገራችን ኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ከወጣበት ከ1986 ዓ.ም. ጊዜ ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ጉልህ ለውጦችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ የዚህ ፖሊሲ ውጤት የሆኑት የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ህልውና ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ በከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በ2000 ዓ.ም. የወጣው የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምህርት ስታቲስቲክስ እንደሚያሳየው 51 መንግስታዊ ያልሆኑ (የግል ተቋማትን ጨምሮ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ከጠቅላላው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብዛት 60 በመቶ) ተቋቁመው በልዩ ልዩ ዘዴዎች ማለትም በመደበኛ፣ በማታ፣ በክረምት እና በርቀት ትምህርት ሥልጠና በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በመንግሥት እና በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የተማሪዎች ብዛት 270,356 ሲሆን ከዚሁ ቁጥር ውስጥ መንግስታዊ ባልሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች ቁጥር 48,802 (ከአጠቃላይ የተማሪዎች ቁጥር 18.1 በመቶ) ነበር፡፡

ይህም የሚያሳየው የግሉ ዘርፍ እየጨመረ የመጣውን የከፍተኛ ትምህርት ፍላጎት እና አቅርቦት ክፍተት ከመሸፈን አኳያ የማይናቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ መሆኑን ነው፡፡ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአበረከቷቸው አስተዋጽኦዎች መካከል የሚከተሉትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

- በርካታ የመማር እድል ተነፍጓቸው የቆዩ ዜጎችን በማሰልጠን እና በማስመረቅ ራሣቸውን እና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ከመደረጉ ባሻገር በአገሪቱ የሰብዓዊ ሀብት ልማት ረገድ የማይናቅ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት ተችሏል፡፡
- መንግስት የተለመውን የከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ የማሳደግ እቅድ አንፃር የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በፈጠሩት እድል በእነዚህ ተቋማት የሴቶች ተሳትፎ ከ 50 በመቶ በላይ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፡፡
- በተለያየ ምክንያት በመንግስት ተቋማት ውስጥ ትምህርታቸውን መከታተል ሳልቻሉ ኢትዮጵያውያን ሰፊ ዕድል መፍጠርና መንግሥትም በራሱ ተቋማት ቢያስለጥን ለዚህ ተግባር ሊያወጣ ይችል የነበረውን ከፍተኛ ወጪ መቀነስ አስችለዋል፡፡


ይሁንና ከእነዚህ አስተዋጽኦዎች ባሻገር በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠውን ትምህርት አግባብነትና ጥራት በተመለከተ መንግሥትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን አስተያየት ወይም ቅሬታ ሲገልጹ ይሰማሉ፡፡ በተቋማቱ ላይ በመንግሥት የተወሰዱና በመወሰድ ላይ ያሉ እርምጃዎችም የመወያያ ጉዳዮች ሆነው ቆይተዋል፡፡

## 2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ወቅታዊ እና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በመመርመርና ከተቋማቱ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ምቹ እና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በመለየት ለፖሊሲ መሻሻል የሚያገለግሉ የመፍትሄ ሃሣቦችን ለመጠቆም ነው፡፡

## 3. የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉትን ወቅታዊ ጉዳዮች ለመመርመር ጥናቱ የሚከተለውን ሞዴል/ ማዕቀፍ ተጠቅሟል፡፡




## 4. የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አምስት ጥያቄዎች ላይ በማተኮር በሃገራችን የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉትን ወቅታዊ ጉዳዮች ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡

ሀ/ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን ፍላጎት ከማሳደግ አኳያ እንዴት እየሠሩ ነው? የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሥልጠና መርሐ-ግብራቸው ጥራትና አግባብነት አንፃር የራሳቸውን ጥቅምና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ሚዛናዊነት ምን ያህል እያስጠበቁ ነው?

ለ/ ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ሲነፃፀር መንግሥት የሚያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦችና፣ ፖሊሲዎች የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንቅስቃሴ ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እያሳደሩ ነው? የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትስ ተፅእኖውን ለመቋቋም (ፖሊሲና ደንቦች የሚጠይቁትን ነገሮች ለማሟላት) ምን አይነት ምላሽ እየሰጡ ይገኛሉ?

ሐ/ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የግልና የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አብሮ የመሥራት /የትብብር ሁኔታ ምን ይመስላል? ከፍተኛ ትምህርትን በሀገሪቱ ከማዳረስ አንፃር በመንግሥትና በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ባለቤቶች መካከል ጤናማ ግንኙነት አለ? ወይንስ የለም ?

መ/ በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራቂ ዎች የሥራ አፈፃፀም ረገድ ቀጣሪ መሥሪያ ቤቶች/ድርጅቶች ምን ያህል ረክተዋል?

ሠ/ በኢትዮጵያ የሚገኙ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያጋጥሟቸው/ ያጋጠሟ ቸው ምቹ ሁኔታዎች እና እንቅፋቶች ምን ምን ናቸው?

## 5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት፣ መልካም አስተዳደር ፣ የሰው ሃይል አመራር ፣ የገንዘብ አያያዝ፣ ወዘተ የማያካ ትት ሲሆን ትኩረቱ ከላይ ከተዘረዘሩት መሠረታዊ ጥያቄዎች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡

## 6. የጥናቱ ዘዴ

የጥናቱን ዓላማዎች ለማሣካት በአገራችን ከሚገኙት የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል አስራ ስድስቱ (ከጠቅላላው 31 በመቶ) ማለትም ሰባት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች (አድማስ፣ አልፋ፣ ሲቲ፣ ቅድስት ማርያም፣ አልካን፣ አፍሪካ ቤዛ፣ ሼባ) ሰባት ኮሌጆች (መካነየሱስ፣ ብሉ ናይል፣ አሌፍ፣ አምቦ፣ ማይክሮ ሊንክ፣ ሉሲ፣ ሆርን) እንዲሁም መቀሌ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ የተመረ°ፈ ሲDን ከመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ስድስት ማለትም (አዲስ አበባ ፣ መቀሌ ፣ አምቦ ፣ ሀዋሣ፣ ሀረማያ እና ባህር ዳር ) ተካተዋል።

ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ማለትም ሀ/ ከላይ በተጠቀሱት የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ 135 መምህራንን፣ 314 ተማሪዎችን እና 72 ተመራቂዎችን የፅሁፍ መጠይቅ በማስሞላት፣ ለ/ ከትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ሃላፊዎች፣ ከስድስቱ ዩኒቨርሲቲዎች የሥራ ኃላፊዎች፣ ከቀጣሪ መሥሪያ ቤቶች/ ድርጅቶች፣ ከወላጆች፣ እና ከኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበር ተወካዮች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ሐ/ የምርምር ፅሁፎችን፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፖሊሲ ዶኩሜንቶችን፣ የጥራት ኦዲት ሪፖርቶችን በማሰባሰብ እና በመመርመር በጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 7. ዋና ዋና ግኝቶችና የማጠቃለያ ነጥቦች

- በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ የሚነሱ አበይት ጉዳዮች ተቋማቱ በሚሠጡት የሥልጠና መርሐ-ግብሮች አግባብነት ላይ ሳይDን በትምህርቱ ጥራት ላይ ያተኮሩ ናቸው።
- የትምህርት ጥራትን በተመለከተ የሚነሱ ችግሮች የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ብቻ የሚመለከቱ አይደሉም። ምክንያቱም ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም መካከል ለመልጣኞቻቸው ጥራት ያለው ትምህርት የማይሠጡ አሉ ።
- በመንግሥት እና በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዘንድ ያለውን ግንኙነት ለማጠናከርም ሆነ የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ያለው ቅርርቦሽ/ትብብር የተጠናከረ አይደለም።
- በመንግሥትና በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለውን ጤናማ ውድድር የሚያበረታቱ የገበያ መርሆች በአግባቡ እየተተ ገበሩ አይደሉም።
- ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ የወጣ አዋጅ ባለመኖሩ የመንግሥትም ሆኑ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚተዳደሩት በአንድ አዋጅ ነው።
- በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ብቻ በእጅጉ ጥብቅ የሆነ ህግና ደንብ ሥራ ላይ ማዋል በሃገሪቱ ወጥ ያልሆነ አሠራር መኖሩን ያሳያል።
- ያልተረጋጋና ወጥነት በሌለው ሁኔታ ያለበቂ ምክክርና ፋታ በየጊዜው መመሪያዎችንና ህጎችን መቀያየሩ፣ ጠንካራና የተቀናጀ የመንግሥት ቁጥጥር ማዕቀፍ ክፍተት መኖሩን ከመጠቆሙም በላይ ስለከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ዋና ሚናና ተልዕኮ ብዥታን ፈጥረዋል።

በአጠቃላይ የተጠናከረና ሁሉን አቀፍ የቁጥጥር ስርዓት/ማዕቀፍ አለመኖር የትምህርትን ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥም ሆነ በተቋማቱ መካከል ጤናማ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ እንቅፋት ሆነዋል።

## 8. የመፍትሔ ሃሳቦች

***የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት:-***

- የሚሠጡት የሥልጠና መርሃ ግብሮች ከሃገሪቱ የሠለጠነ የሠው ሃይል ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፣ አቅምን ያገናዘበና ደረጃውን

የጠበቀ እንዲሁም የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ለብሔራዊ እድገት ፋይዳ ያለው ቢሆን ፣

- የመምህራንንና ሠራተኞቻቸውን ሙያ ለማዳበር ሲያቅዱም ሆነ ሲተገብሩ ከትምህርት ሚኒስ ቴር፣ ከሌሎች የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ምክክር ማድረግ፤ እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ የሥልጠና መርሃ ግብራቸውን አግባብነትና ጥራት በየጊዜው የመገምገም ተቋማዊ የአሠራር ባህል ማጸበር ያስፈልጋል::

***የኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበር:-***

- የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የሥራ አፈፃፀም ብቃት ለማሻሻልና የወደፊት እጣፋን ታቸውን በዘላቂነት ለማረጋገጥ ያስችለው ዘንድ በትምህርት ጥራት ቁጥጥር፣ እውቅናን በመሥጠትና በመሣሠሉት ሥራዎች ንቁ ተሳትፎ ቢያደርግ፤ ብሎም ከመንግሥት፣ ከአሰሪዎች፣ ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህ ርት ተቋማትና መሠል የሙያ ድርጅቶች ጋር በቅርበት ቢሰራ፣
- የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉባቸውን ድክመቶች የሚለዩበት እንዲሁም የሥልጠና ፕሮግራሞቻቸውን አግባብነትና ጥራት የሚያሻሽሉበት መድረክ ሆኖ ቢያገለግል፣

***መንግሥት (ትምህርት ሚኒስቴር/ የትምህርት እና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ):-***

- የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ልማት ውስጥ የትምህርት ተደራሽነትን በማሳደግና የሠለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት ረገድ ያላቸውን አስተዋፅኦ ቢያበረታታ፣
- ለመንግሥትም ሆነ ለግል ትምህርት ተቋማት በጋራ የሚያገለግል ተቋማዊ ነፃነት ያለው ኤጀንሲ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ የቁጥጥር መዋቅር/ማዕቀፍ እንዲኖር ቢያደርግ፣
- የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን አቅም ለመገንባትና በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ሃይል ችግራቸውን ለማሟላት እንዲችሉ የከፍተኛ ትምህርት ሥልጠና ዕድል ኮታ (ከ20-30 በመቶ) ለተቋማቱ ቢሰጥ፣
- የኬንያን ተሞክሮ በመውሰድ አሁን በሥራ ላይ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪ ዎችን ምደባ መመሪያ በማሻሻል ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት መመዘኛዎቹን የሚያሟሉ ተማሪዎች በመንግሥት ድጋፍ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡበት ሁኔታ ቢፈጠር፣

የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ሁሉንም የሃገሪቱን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያበረታታ፣ ጤናማ ውድድር የሚፈጥር፣ የጋራ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ ቢሆን፣ ለዚህም የመንግሥትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትብብር ፎረም እንዲቋቋም ቢደረግ በግሉ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል::

**ወሰኑ ይማም (ዶ/ር)**

**ሙሉ ነጋ (አቶ)**

***<u>ምንጭ</u>***:- Wossenu Yimam and Mulu Nega. 2010. “Current Issues in Ethiopian Private Higher Education Institutions: Opportunities and Challenges,” a study commissioned by Forum for Social Studies (FSS), Addis Ababa.

<u>ምስጋናና ማሳሰቢያ</u>

ይህ ሰነድ የታተመው በለጋሾች ቡድን የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲያኑ ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሾች ቡድንን ወይም የአሳታሚውን አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም::

አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ፣ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
❄ ስልክ 011-629 78 88/91 ❄ ፋክስ 011-629 78 89
❄ ኢሜይል: fss@ethionet.et ❄ ድረ-ገፅ www.fssethiopia.org.et